# ነገረ-መለኮታዊ መሠረቶች

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ
**ነገረ-መለኮትህን መገንባት**

**የኮርሱ መግለጫ**

ለሁለት ምዕተ-ዓመታት ያህል፣ በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ ሰብሰብ ብለው የተቀመጡ ማዕከላዊ የእምነት አቋሞች በክርስቲያኖች ዘንድ ይስተዋሉ ነበሩ፡፡ በተመሳሳይ መንገድም፣ የወንጌላውያኑ ነገረ-መለኮት በግጭት በተሞሉ አመለካከቶች ተጥለቀለቀ፡፡ ከእነዚህ አለመስማማቶች መካከል አብዛኞቹ በቤተእምነቶች መካከል፣ የተቀሩት ደግሞ በቤተእምነቶችና በአጥቢያ ቤተክርስቲያናት መካከል የሚነሱ ነበሩ፡፡ ቢያንስ ለመነሻ ያህል በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ላይ በተቀመጠው መንገድ እንኳን ነገረ-መለኮታዊ አንድነትን የማምጣቱ ነገር ተስፋ የሌለው የመሆኑ ነገር ግልጽ በመሆኑ አንዳንድ ክርስቲያኖች የነገረ-መለኮትን ጉዳይ ዋጋ ቢስ አደረጉት፡፡ ታማኝነታችንን የምንለካባቸው በርካታ ተፎካካሪ ሃሳቦች እያሉ፣ የኢየሱስ ተከታዮች ሊከተሉ የሚገባቸውን እንዴት ይለዩ? እኛስ ለአንዳንድ አስተምህሮዎች እና ትውፊቶች ራሳችንን ልንሰጥ የምንችለው እንዴት ነው? ኮርሱም በእነዚህ ሁለት ሞጋች ጥያቄዎች ላይ እንድታሰላስሉ የሚያግዛችሁ ሲሆን፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫና ነገረ-መለኮትህን መገንባት በሚሉ፣ በዶ/ር ቫን ጋይተን እን ዶ/ር ቪንሰንት ባኮቴ እና ከተለያዩ ፕሮፌሰሮች ከተሰባሰቡ ሃሳቦች በተዘጋጁ ሁለት ቪዲዮዎች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

**ግቦችና ዓላማዎች**

*ግቦች*

በዚህ ኮርስ፣ የሚከተሉትን ማሳካት እንፈልጋለን:

1. *የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫን ወሳኝ ታሪካዊ መሠረቶች እንደምትረዱና በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ የተጠቀሱትን አስትምሮዎች ትርጉሞች ትረዳላችሁ ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡*
2. *የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ለዘመናችን ቤተክርስቲያን ያለውን ዋጋ በአግባቡ ትረዳላችሁ ደግሞም በውስጡ የተገለጡትን አስተምህሮዎች ታምናላችሁ ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡*
3. *እግዚአብሔርን እንደ አባታችሁ፣ ኢየሱስን እንደ አዳኛችሁ፣ መንፈስ ቅዱስን እንደ መሪያችሁ በማመን፣ በኮርሱ ውስጥ የሚገኙትን ትምህርቶች በልባችሁና በሕይወታችሁ ተግባራዊ በማድረግ፣ በጸጋ ትኖራላችሁ ደግሞም በቤተክርስቲያን ውስጥ ተሳታፊ ትሆናላችሁ ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡*
4. *የነገረ-መለኮትን ባህርይና ዓላማ ትረዳላችሁ ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡*
5. *ለነገረ-መለኮት አዲስ ፍቅር እንደምታዳብሩ፣ ደግሞም ከቅዱሳት መጻሕፍት በሚመነጭ መንገድ ልባችሁን እና ሕይወታችሁን የሚለውጥ ነገረ-መለኮት ታዳብራላችሁ ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡*
6. *ከዚህ ትምህርት ላገኛችሁት ትምህርት ምላሽ በሚሆን መንገድ በሕይወታችሁ ለውጥ እንደምታሳዩ ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ኦርቶዶክሲን፣ ኦርቶፕራክሲስን እና ኦርቶፓቶስን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነገረ-መለኮትን የምትመሠርቱበትን ደግሞም ነገረ-መለኮታዊ መግለጫዎችን የምትመረምሩበትን መንገድ ሊለውጠው ይገባል፡፡*

*ዓላማዎች*

ከታች የተዘረሩትን ካከናወናች፣ ግቦቻችን የተሳኩ መሆኑን ያሳያል:

1. አውቶማቲካዊ በሆነ መንገድ ማርክ በሚሰጣቸው የኮርሱ ክፍሎች አጥጋቢ ውጤት ይኑራችሁ፣ ያም የሚከተሉትን ማድረግ እንደምትችሉ ያሳያል:
    - የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫን ታሪክ ቁልፍ መረጃዎች መለየታችሁን፣
    - በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ የተገለጹትን አስተምህሮዎች ትርጓሜ መለየታችሁን፣
    - ነገረ-መለኮትን የምታጠኑበትን ቁልፍ ምክንያት መረዳታችሁን፣
    - በነገረ-መለኮት ሥራ ውስጥ የኦርቶዶክሲን፣ የኦርቶፕራክሲስን እና የኦርቶፓቶስን ወሳኝነት ለይታችሁ ማወቃችሁን፣
    - ወሳኝ የሆኑ የነገረ-መለኮት ምሁራንን ቁልፍ ሃሳቦች መለየታችሁን፣
    - ነገረ-መለኮትን በማዘጋጀት ረገድ የተለያዩ መገለጦችንና ያላቸውን ወሳኝነት መለየታችሁን፣
    - በእስትንፋሰ መለኮት ረገድ ያሉ የተለያዩ አመለካከቶችንና የቅዱሳት መጻሕፍት ትክክለኛ አተረጓጎሞችን ለይታችሁ ማወቃችሁን፣
    - የሪፎርምድ ቲዮሎጂን ቁልፍ አጽንዖት የሚያደርግባቸውን ትኩረቶች መለየታችሁን
2. ስለ ሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ እና ስለ አስተምህሮዎቹ ያላችሁን አስተሳሰብ በመግለጥ፣ ከእግዚአብሔር አብ፣ ከኢየሱስ፣ እና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያላችሁን ግንኙነት በመግለጥ፣ በጸጋ መኖራችሁን እና በቤተክርስቲያን ውስጥ ተሳትፎ ማድረጋችሁን በመግለጥ፣ ስለ ነገረ-መለኮት ያላችሁን አስተሳሰብ በማንጸባረቅ፣ በኮርሱ ውስጥ ያገኛችሁትን አስተምህሮ በሕይወታችሁ ተግባራዊ ማድረጋችሁን በማሳየት፣ በተለይ ደግሞ ነገረ-መለኮትን በመገንባትና ነገረ-መለኮታዊ ትንታኔዎችን በመመርመር፣ የኦርቶዶክሲን፣ የኦርቶፕራክሲስን እና ኦርቶፓቶስን ገጽታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የኮርሱን የጥናት መምሪያዎች አጠናቅቁ፡፡

**በመሪ ሃሳቦች ላይ ያተኮረ የኮርሱ አስተዋጽዖ**

1. የእምነት አንቀጽ
2. እግዚአብሔር አብ
3. ኢየሱስ ክርስቶስ
4. መንፈስ ቅዱስ
5. ቤተክርስቲያን
6. ድነት
7. ነገረ-መለኮት ምንድን ነው?
8. ክርስቲያናዊ ነገረ-መለኮትን መመርመር
9. በመገለጥ ላይ መደገፍ
10. ሥልጣንና ነገረ-መለኮት

**የቤት ሥራዎቹ ማብራሪያ**

*የብዝሃ መገናኛ ትምህርቶች*

1. **ትምህርቶቹን** ማጥናት፣ ቪዲዮዎቹን መመልከት፣ ኦዲዮዎችን ማድመጥ፣ ወይም ምንባቡን ማድመጥ፡፡
2. ለየትምህርቶቹ የተሰጡትን **የጥናት መምሪያዎች** አጠናቅቁ፡፡ እነዚህ የጥናት መምሪያዎች ለኦንላይን ፈተናዎች የሚያዘጋጇችሁ ሲሆን የትምህርቶቹን አስተምህሮዎች በግል ሕይወታችሁ እንድታዛምዱ ያግዟችኋል፡፡
3. ለየትምህርቶቹ የተሰጡትን የኦንላይን **ፈተናዎች** ውሰዱ፡፡ ፈተናዎቹን የፈለጋችሁትን ያህል ደጋግማችሁ መውሰድ ትችላላችሁ፣ በእያንዳንዱ ሙከራችሁ መካከል ግን ለአንድ ሰዓት መጠበቅ ይኖርባችኋል፡፡ ያመጣችሁት ከፍተኛ ነጥብ በይፋ የሚመዘገብ ውጤታችሁ ይሆናል፡፡ ጽንሰ-ሃሳቦቹን በትክክል መረዳታችን ለማረጋገጥ በሳምንታዊ ውይይት ላይ ተሳታፊ ከመሆናችሁ አስቀድሞ ቢያንስ 80% ውጤት ብታስመግቡ መልካም እንደሚሆን እንመክራለን፡፡
4. የየትምህርቶቹን የውይይት መምሪያ በመጠቀም፣ ከቡድናችሁና ከአሰልጣኞቻችሁ ጋር በሚደረገው ሳምንታዊ ውይይት ተሳተፉ፡፡ ውይይቶቹ በኮርሱ ውስጥ የተቀመጡትን ሃሳቦች በትክክል መረዳታችሁን እና ጽንሰ-ሃሳቦቹንም በሕይወታችሁና በአገልግሎታችሁ በትክክል ተግባራዊ የማድረግ አቅማችሁን ለማሳደግ ወሳኝ ናቸው፡፡ በቪዲዮ በሚቀርቡ ትምህርቶች ላይ የሚደረገው ውይይት ለአንድ ሰዓት ያህል ቢዘልቅ እንመክራለን፡፡
5. ***የነገረ-መለኮታዊ መሠረቶችን* - *የፍጻሜ ፈተና*** ውሰዱ፡፡ ለክለሳ ይረዳችሁ ዘንድ የፈለጋችሁትን ያህል ደጋግማችሁ መውሰድ ትችላላችሁ፣ ሆኖም በሙከራዎቻችሁ መካከል የአንድ ሰዓት ገደብ ስጡ፡፡ ያመጣችሁት ከፍተኛ ነጥብ ይፋ ውጤታችሁ ይሆናል፣ ወደሚቀጥለው ኮርስ ከመሸጋገራችሁ አስቀድሞ ግን ቢያንስ 80% ውጤት እንዲኖራችሁ እንመክራለን፡፡

*የጸሎት ባጅ*

1. በየሳምንቱ ለአንድ ሰዓት ያህል **በጸሎት ባጁ *መመሪያዎች*** መሠረት የምትሠሩበት ጊዜ ሊኖር ይገባል፡፡ ይህ ባለ አንደ ወይም ሁለት ገጽ መምሪያ ይህንን ወሳኝ የአገልግሎት ክህሎት ለማሳደግ በምትጥሩበት ወቅት አሰልጣኞቻችሁ ተገቢ እገዛ እንዲያደርጉላችሁ የሚያስችለውን አጠቃላይ አቅጣጫ ይጠቁመዋል፡፡
2. በመጀመሪያዎቹ ሳምንታት፣ በወንጌል ተልዕኮ ባጅ መመሪያዎች ላይ በተቀመጡት ***የመወያያ* ርዕሶች ላይ** ለአንድ ሰዓት ያህል ቆይታ አድርጉ፡፡
3. በቡድን ውይይት ክፍለ ጊዜ አስተማማኝ መሠረት ከተጣለ፣ በተቀሩት ሳምንታት **በተግባራዊ ርምጃዎች** ባጅ ላይ ቆይታ አድርጉ፡፡
4. አሰልጣኞቻችሁ በባጁ መመሪያዎች መሠረት ተግባራዊ እርምጃዎቹን መውሰዳችሁን ማረጋገጫ ከሰጠ፣ የባጅ ሽልማት ትቀበላላችሁ፡፡ ሁሉም ባጆች በተማሪ  በኦንላይን የትምህርት ክፍል “የመረጃ ቋት” ውስጥ በግልጽ ይቀመጣሉ፡፡

**ነጥቦች**

የመጨረሻው ውጤት የሚሰላው በሚከተለው መንገድ ነው:

1. በሌክቸሮቹ ላይ የሚሰጠው ፈተና 30 ነጥቦችን ይይል፡፡
2. በሌክቸሮቹ ላይ የሚሰጠው የመጨረሻ ፈተና 100 ነጥቦችን ይይል፡፡
3. የጸሎት ባጅ ሪፖርቱ በውጤታችሁ ላይ የሚያመጣው ለውጥ አይኖርም ሆኖም ኮርሱን ማጠናቀቃችሁን ለማረጋገጥ ተጠናቅቆ ሊቀርብ ይገባዋል፡፡

*ከ80% በላይ ውጤት የተመዘገበበት ኮርስ እንደታለፈ ይቆጠራል፡፡*